# ምዕራፍ ዘጠኝ

# መንፈስ ቅዱስ ማነው?

ስለመንፈስ ቅዱስ ማንነት ማወቅ የሚገባንን ያህል ለማወቅ በእውቀት ምንጭነት የሚያገለግለው መጽሐፍ ቅዱስ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለመንፈስ ቅዱስ ማንነት ሲያስተምር መንፈስ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ተብለው ከሚመሰገኑት ከሦስቱ መለኮታውያን አካላት (አካላተ መለኮት) አንዱ እንደሆነ እና ለምልዓተ መለኮቱ ወሠን የሌለው ከአብ ከወልድ ጋር በአንድነት የሚሰገድለት የሚመለክ ዕሩየ መለኮት የሆነ አካላዊ መንፈስ ባሕርያዊ እስትንፋስ ነው። በነቢያት አድሮ የተናገረ ፍጹም አካል ያለው አዳኝ ጌታ ነው፤ እንዲሁም በአንድነት በሦስትነት ዓለምን የፈጠረ አምላክ ነው ይለናል።

ከዚህ በኋላ ስለመንፈስ ቅዱስ ማንነት ስለስሞቹ፣ ስለተመሰለባቸው ምሳሌዎች መንፈስ ቅዱስ ወደዓለም ስለወረደበት ዓላማ እንዴት ወደዓለም እንደወረደ በሕይወታችን ምን እንደሚሠራ፣ መንፈስ ቅዱስ ስለተመሰለባቸው ምሳሌዎች፣ የመንፈስ ቅዱስ አካላዊነት ስለተገለጸባቸው አካላዊ ቋንቋዎችና መንፈስ ቅዱስ ከሕይወታችን እንዳይለይ ስለምናደርጋቸው ጥንቃቄዎች በቅደም ተከተል እንመለከታለን።

## ማነው?

### 1. መንፈስ ቅዱስ ፈጣሬ ዓለማት ገባሬ ዓለማት ነው።

ይህንን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ "ወመንፈሰ እግዚአብሔር ይጼልል መልዕልተ ማይ ማለትም የእግዚአብሔር መንፈስ በውኃ ላይ



ሰፍፎ ነበር" ይላል (ዘፍ 1፥2) (የዓለም ሁኔታ) ሳይጸና ምድር እንደውኃ በምትዋልልበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ያዘጋጃት ነበር። ባልጸናችው ምድር ላይ የመንፈስ ቅዱስ መንሳፈፍ በአንዲት የበረኃ ወፍ ታቅፎ ያልረጋው እንቁላል ረግቶ ጫጩት እንደሚሆን እንደዚሁ መንፈስ ቅዱስ በባሕር ላይ በመስፈፍ ያልጸናውን ዓለም እንዲጸና አድርጎታል። ዘማሪውም "በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ" (መዝ 3፥6) በማለት የምድርና የሠማይ ሠራዊት በአካላዊ እስትንፋስ እንደጸኑ ይነግረናል። ኢዮብም በበኩሉ "የእግዚአብሔር መንፈስ ፈጠረኝ ሁሉንም የሚችል የአምላክ እስትንፋስ ሕይወትን ሰጠኝ" (ኢዮ 33፥4) በማለት በአካላዊ እስትንፋስ አብ ወወልድ በባሕርያዊ ሕይወተ አብ ወወልድ ሕይወትን ሰው ሁሉ እንደለበሰ ይነግረናል። ይህም እውነታ "እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ" (ዘፍ 2፥7) ተብሎ ከተጻፈው ጋር ይስማማል። በመሆኑም መንፈስ ቅዱስ ከአብ ከወልድ ጋር በአንዲት መለኮታዊት ክሂል ዓለምን ያሆነ፣ ያደረገ፣ የፈጠረ፣ ፈጣሪ፣ ገባሪ፣ ሕያው ጌታ ነው።

### 2. መንፈስ ቅዱስ ከአብ ከወልድ ጋር ዕሩየ መለኮት በመሆኑ እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር ይባላል እግዚአብሔር ስሙ ነው፤

መጽሐፍ ቅዱስም እግዚአብሔር በማለት ከአብ ከወልድ ጋር ያለውን ዕሪና፣ እግዚእና፣ ዕሩየ መለኮትነት ይጠቁማል። በትንቢተ ኢሳይያስ 6፥1-10 እግዚአብሔር ተብሎ የተጠራው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ሐዋርያው ቅ/ጳውሎስ ቁልጭ አድርጎ ተርጉሞታል (የሐዋ 28፥23-28) ቅ/ጴጥሮስም እግዚአብሔር ብሎ እንደጠራው በሐዋ 5፥3-4 ማንበብ እንችላለን።

## 3. ከአብና ከወልድ ጋር ዋህደ መለኮት ፅሩየ መለኮት ቢሆንም ልዩ አካል ነው፤

ለአብ የራሱ የሆነ አካል አለው፣ አብ የሚለው ስሙም ስመ አካል ነው፣ ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል አብ ይባላል። ወልድም የራሱ የሆነ አካል አለው፣ ከሦስቱ አካላት አንዱ ወልድ ይባላል፤ መንፈስ ቅዱስም የራሱ የሆነ አካል አለው፣ ከሦስቱ አካላት አንዱ መንፈስ ቅዱስ ይባላል። መንፈስ ቅዱስም ስመግብር ስመኩነት ያይደለ ስመ አካል ነው።

ይህንንም ትምህርት መጽሐፈ ሕይወት ባሕረ ጥበብ መጽሐፍ ቅዱስ በአሜፋሪ ወይንም በመስተጻምር እንደሚከተለው ይገልጸዋል። “አሁንም ጌታ እግዚአብሔርና መንፈሱ ልከውኛል” (ኢሳ 48፥16) ይህ ቃል የመንፈስ ቅዱስን አካላዊነት ይገልጻል ጌታ እግዚአብሔር የተባለው አብ ሲሆን በመስተጻምር መንፈሱ ተብሎ የተጠቀሰው መንፈስ ቅዱስ ነው። ልከውኛል የሚለው ቃለ ትንቢት ደግሞ በሥጋ ማርያም የተገለጸውን ኢየሱስ ክርስቶስን ይጠቁማል። “እስመ በፈቃዱ ወበሥምረተ አቡሁ ወመንፈስ ቅዱስ መጽአ ወአድኃነነ - በእርሱ ፈቃድ በአባቱ ፈቃድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ፈቃድ መጥቶ አዳነን” እንዳለ ሊቁ (የማክሰኞ ውዳሴ ማርያም) (ማቴ 28፥19)

## 4. በስሙ ልዩ ነው፤

እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ተለይቶ የሚጠራበት አካላዊ ስሙ መንፈስ ቅዱስ ነው። በመሆኑም በስሙ ልዩ ነው፣ መንፈስ ቅዱስ አካላዊ በመሆኑ መንፈስ ቅዱስ ይባላል። መንፈስ ቅዱስ ስመ አካል ነው ይህ ስም የመንፈስ ቅዱስ መጠሪያ ስም ነው፤ መቼም መች በዚህ ስም አብ - ወልድ አልተጠሩበትም፣ ስመ አካለ ወልድ ወልድ ነውና አብ - መንፈስ ቅዱስ አይጠሩበትም፣ አብም የአብ ስም ብቻ ነው የወልድ- የመንፈስ ቅዱስ ስም አይደለም በዚህም ስም



ወልድ መንፈስ ቅዱስ አልተጠሩበትም፣ አይጠሩበትም። ስመ አካለ - አብ ነውና። ሥላሴ (አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ) ግን አካላቸው ስማቸው የተለየ ቢሆንም ባሕርያቸው ተከፍሎ የሌለበት አንድ ነው።

አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ተብለው የሚጠሩ እግዚአብሔራውያን ሦስቱ አስማተ አካላት ግን አይፋለሱም ይህን በተመለከተ ሊቁ አግናጥዮስ የተናገረውን ቃል እንመልከት “አብ ውእቱ አብ ኢኮነ ወልደ ወኢመንፈስ ቅዱሰ፣ ወልድኒ ውእቱ ወልድ ወኢኮነ አበ ወኢመንፈስ ቅዱሰ፣ መንፈስ ቅዱስኒ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ኢኮነ አበ ወኢወልደ፣ አብ ኢይፈልስ ለከዊነ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ወኢወልድ ለከዊነ አብ ወመንፈስ ቅዱስ ወኢመንፈስ ቅዱስ ለከዊነ አብ ወወልድ” ትርጉሙ “አብ እርሱ አብ እንጂ ወልድ ወይም መንፈስ ቅዱስ አይደለም። መንፈስ ቅዱስም እርሱ መንፈስ ቅዱስ እንጂ አብ ወይም ወልድ አይደለም፤ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ወደመሆን አይለወጥም ወልድም አብ መንፈስ ቅዱስ ወደመሆን አይለወጥም መንፈስ ቅዱስም አብ ወልድ ወደመሆን አይለወጥም” በማለት ተናግሯል (ሃይማኖተ አበው ዘአግናጥዮስ ዘአንጾኪያ ገጽ 37 ክፍል 1 ቁ. 8-9) ሦስቱ የእግዚአብሔር አካላት አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ፍጹማንና ምሉዓን አካላት መሆናቸውን በብቃት ያስገነዘበው ገለጻ አብ ልብ ሲሆን በልብነቱ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ኅሊናቸው በመሆኑ እንደሆነ ወልድም ቃል ሲሆን በቃልነቱ ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው ንግግራቸው በመሆኑ እንደሆነ መንፈስ ቅዱስም እስትንፋስ ሲሆን በእስትንፋስነቱ ለአብና ለወልድ እስትንፋሳቸው እንደሆነ ወይንም ሕይወታቸው በመሆኑ እንደሆነ የቤተክርስቲያን አበውም ሆነ የውሉደ አበው ምዕመናን መሠረታዊና ኦርቶዶክሳዊ እምነት ነው።

## 5. ሠራፂ ነው፤

መንፈስ ቅዱስ ቅድመ ዓለም ወልድን ከወለደ ከአብ ቅድመ ዓለም ስለሠረፀ ሠራፂ ይባላል። ይህም ሠራፂ የተሰኘው ስሙ ከሦስቱ አስማተ አካላተ መለኮት አንዱ መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ከሦስቱ አስማተ ግብር አንዱ ነው ሠራፂ የሚለው ስሙም ስመ አካል ስመ ኩነት ያይደለ ስመ ግብር ነው። የመንፈስ ቅዱስ ስመ ግብር ሠራፂ ነው። የወልድ ተወላዲ የአብ ወላዲ አሥራፂ ስመ ግብራቸው እንደሆነ ሁሉ።

መንፈስ ቅዱስ የሚሠርፀው ከአብ ብቻ ነው ይህንንም እውነት መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚከተለው ይገልጸዋል "ወሶበ መጽአ ጰራቅሊጦስ ዘአነ እፌኑ ለክሙ እምኀበ አብ መንፈሰ ጽድቅ ዘይወፅእ እምኀበ አብ ውእቱ ሰማዕትየ።" ሲተረጎም "እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ ከአብ የሠረፀ (የወጣ) መንፈስ ቅዱስ በመጣ ጊዜ ስለእኔ ይመሰክራል" ማለት ነው (ዮሐ 15፥26) በዚህ መለኮታዊ ቃል መሠረት 318ቱ ሊቃውንትና መሰሎቻቸውም "ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ እግዚእ ማኅየዊ ዘሠረፀ እምአብ ንስግድ ሎቱ ወንሰብሖ ምስለ አብ ወወልድ ዘነበበ በነቢያት" ሲተረጎም "ከአብ በሠረጸ ከአብና ከወልድ ጋር በነቢያት አድሮ በተናገረ በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን እንሰግድለት እናመሰግነውም ዘንድ" (ጸሎተ ሃይማኖት ዘኒቅያ) ብለው አቋማቸውን ገልጸዋል።

ኤጲፋንዮስ ኤጲስ ቆጶስ ዘቆጵሮስ ደግሞ "ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ ዘነበበ በኦሪት ወተሰብከ በነቢያት ወነበበ በሐዋርያት ወወረደ በዮርዳኖስ ውኀደረ በቅዱሳን ወከመ፤ ነአምን ከመ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ መንፈስ ፍጹም ጰራቅሊጦስ እምአብ ዘይወጽእ እምወልድ ዘይነሥእ" ትርጓሜው፡- በኦሪት በተናገረ፣ በነቢያት በተሰበከ፣ በሐዋርያት ባስተማረ፣ በዮርዳኖስ በወረደው በቅዱሳን ባደረው በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን እንደዚሁ ይህ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር መንፈስ ጰራቅሊጦስ



የሚባል ፍጹም መንፈስ እንደሆነና ከአብ የሚወጣ ከወልድ የሚወስድ እንደሆነ እናምናለን። ብሎአል።

## 6. አጽናኝ ነው፤

መንፈስ ቅዱስ እረኛቸውን ላጡት በጎች ሰብሳቢ፣ ከኢየሱስ ክርስቶስ ተለይቶ መቆየት ለማይቻላት ቤተክርስቲያን አበረታች፣ ሞት፣ ሕመም፣ ኃዘን፣ ልዩ ልዩ ጸዋትወ መከራ ላጠቃቸው ደቂቀ አዳም አጽናኝ በመሆኑ በግሪክ ጰራቅሊጦስ ይባላል። አማርኛው መጽሐፍ ቅዱሳችንም "እኔም አብን እለምናለሁ ለዘለዓለም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል።" (ዮሐ 14፥16) እንዲሁም "ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለእኔ ይመሰክራል።" ይላል (ዮሐ 15፥26) በተጨማሪ ዮሐ 16፥5-15 ይመልከቱ።

## 7. የመንፈስ ቅዱስ ስሞች፤

መንፈስ ቅዱስ ከልዩ ልዩ መናፍስት የሚለይባቸው ልዩ ልዩ ማንነቱን የሚገልጹ ስሞች አሉት እነዚህንም ስሞች በቅደም ተከተል እንመለከታቸዋለን።

### 7.1 የእውነት መንፈስ፤

በዓለም ካሉ መናፍስተ ሐሰት ለመለየት መንፈስ ቅዱስን የእውነት መንፈስ ይለዋል። በቃለ እግዚአብሔር የእውነት መንፈስ ማለት ወደእውነት ለመምራት የሚችል በእውነት ለመኖር የሚያበቃ በመሆኑ የእውነት መንፈስ ይባላል። ጌታም በመዋዕለ ሥጋዌው "ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል

የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይናገርምና የሚመጣውንም ይነግራችኋል" በማለት ነው ይህንኑ ያስተማረን (ዮሐ 16፥13)

## 7.2 የቅድስና መንፈስ፤

መንፈስ ቅዱስን ከርኩስ መንፈስ በመለየት ሰዎችን በነፍስ በሥጋ እንደሚቀድስ ለመግለጽ የቅድስና መንፈስ ይባላል። ስለዚህም ቅ/ጳውሎስ "ይህም ወንጌል በሥጋ በዳዊት ዘር ስለተወለደ እንደ ቅድስና መንፈስ ግን ከሙታን መነሣት የተነሣ በኃይል የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ስለተገለጠ ስለ ልጁ ነው። እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።" በማለት ያብራራልናል (ሮሜ 1፥4)

## 7.3 የሕይወት መንፈስ፤

የዚህ ዓለም ገዳይ ከሆነው መንፈስ ርኩስ ሰዎችን ወደሕይወት ሳይሆን ወደሞት ካሰማራ ርኩስ መንፈስ ለመለየት መንፈስ ሕይወት ይባላል ሰዎችንም ወደሕይወት፣ ለሕይወት፣ በሕይወት ይመራናልና ነው በመሆኑም "በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ግን ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና" (ሮሜ 8፥2) ይላል ቅ/ጳውሎስ።

## 7.4 የክርስቶስ መንፈስ የእግዚአብሔር መንፈስ ይባላል፤

ይህ አባባል የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት ግልጽ የሚያደርግ አባባል ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ ያለውን የክርስቶስ፤ የክርስቶስ ያለውን የእግዚአብሔር መንፈስ ስለሚል ነው። ይህ ስያሜም መንፈስ ቅዱስ ሕይወተ አብ ወወልድ መሆኑን ይገልጻል። ሐዋርያውም "እናንተ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደላችሁም" ይላል (ሮሜ 8፥9) በተጨማሪ 1ቆሮ 3፥16 ይመልከቱ።



## 7.5 የእምነት መንፈስ፤

ከኑፋቄ መንፈስ፣ ከጥርጥር መንፈስ፣ ከመንፈስ ካህድ ለመለየት መንፈስ አሚን (የእምነት መንፈስ) ይባላል። በሌላም በኩል እምነታችን የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ስለሆነ ነው። (ገላ 5፥22-23) "ነገር ግን አመንሁ ስለዚህም ተናገርሁ ተብሎ እንደተጻፈ ያው አንዱ የእምነት መንፈስ ስላለን እኛ ደግሞ እናምናለን ስለዚህም እንናገራለን።" (2ቆሮ 4፥13) የሚለው ቃልም ይህንኑ ነው የሚያስተምረው።

## 7.6 መንፈስ ጥበብ፤

በዓለም ካለው አእምሮን ከሚያደነዝዝ ዓለማዊ መንፈስ ለመለየት መንፈስ ጥበብ መንፈስ ክስተት ይባላል። የሚከተለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃም ይህንኑ ግልጽ የሚያደርግ ነው። "የክብር አባት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እርሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ።" (ኤፌ 1፥17) በማለት ቅ/ጳውሎስ እንደጸለየ።

## 7.7 መንፈስ ኃይል ወፍቅር ነው፤

ከድካም መንፈስ ከመንፈስ ተቃርኖ በመለየት የኃይል መንፈስ፣ የፍቅር መንፈስ፣ ራስን የመግዛት መንፈስ ይባላል። "እግዚአብሔር የኃይልና የፍቅር ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሃት መንፈስ አልሰጠንምና" የሚለው ቃልም ከዚሁ ጋር አብሮ የሚሄድ ነው። (2ጢሞ 1፥7)

## 7.8 የዘለዓለም መንፈስ፤

ከፍጡር መንፈስ ከሚኖረው መንፈስ ከሚለወጠው መንፈስ ለመለየት የዘለዓለም መንፈስ ይባላል። "ነውር የሌለው ሆኖ በዘለዓለም መንፈስ ራሱን ለእግዚአብሔር ያቀረበ የክርስቶስ ደም እንዴት ይልቅ

ሕያውን እግዚአብሔር ልታመልኩ ከሞተ ሥራ ኅሊናችሁን ያነጻ ይሆን?" ተብሎ ተጽፏልና። (ዕብ. 9፥14)

## 7.9 መንፈሰ ጸጋ፣ (የጸጋ መንፈስ) ይባላል፤

ሌሎች መናፍስተ ሐሣር ወንድዮት ስላሉ ከነዚያ ለመለየት መንፈሰ ጸጋ ይባላል። ሀብታተ አብያተ ክርስቲያናት የመንፈስ ሥጦታዎች ናቸውና "የእግዚአብሔርን ልጅ የረገጠ ያንንም የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም እንደርኩስ ነገር የቆጠረ የጸጋውንም መንፈስ ያክፋፋ እንዴት ይልቅ የሚብስ ኃጢአት የሚገባው ይመስላችኋል?" ተብሎ ተጽፎአል (ዕብ 10፥29)

## 7.10 የክብር መንፈስ ይባላል፤

ሰዎችን ሁሉ ወደ ውርደት፣ ወደሐሣር፣ ወደ መከራ የሚመራ መንፈሰ ሐሣር ወርዶአልና ከዚያ ሲለይ መንፈሰ ክብር ይለዋል። "ስለክርስቶስ ስም ብትነቀፉ የክብር መንፈስ የእግዚአብሔርም መንፈስ በእናንተ ላይ ያርፉልና ብፁዓን ናችሁ።" (1ጴጥ 4፥14) የሚለው መለኮታዊ ቃል ይህንኑ ነው የሚገልጽልን።

# 8. መንፈስ ቅዱስ ለምን ወደ ዓለማችን በበዓለ ሃምሣ ወረደ፤

## 8.1 ኃይልን ለመስጠት፤

ድኩማን ኃይል ደቂቀ አዳም ይህን ዓለም በወንጌል ለመለወጥ ከአርያም ኃይል ያስፈልጋቸው ስለነበር ኃይልን ሊያለብሣቸው ነው የወረደው "እነሆም አባቴ የሰጠውን ተስፋ እኔ እልክላችኋለሁ እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ" እንዳለ መድኃኒታችን፤ (ሉቃ 24፥49) በተጨማሪ የሐዋ 1፥8 ይመልከቱ።



## 8.2 ሐሰተኛውን ዓለም ለመውቀስ፤

"እርሱም መጥቶ ስለኃጢአት ስለጽድቅም ስለፍርድም ዓለምን ይወቅሳል ስለኃጢአት፣ በእኔ ስለማያምኑ ነው፣ ስለጽድቅም ወደአብ ስለምሄድ ከዚህም በኋላ ስለማታዩኝ ነው፣ ስለፍርድም የዚህ ዓለም ገዥ ስለተፈረደበት ነው።" (ዮሐ 16፥8-12) ተብሎ እንደተጻፈ።

አዎን በእውነተኛው ጌታ አለማመን፣ ድል ስለተነሣው ጠላት ውድቀት አለማወቅ በኢየሱስ ክርስቶስ ወደቀደመ ክብር መመለስን አለማመን በደል ስለሆነ ይህንኑ ግልጽ አድርጎ ለመውቀስ ነው የመጣው።

## 8.3 ወደእውነት ሰዎችን ለማድረስ (ለመምራት)፤

"ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይናገርምና የሚመጣውንም ይነግራችኋል" ይለናል ጌታ (ዮሐ 16፥13) ዘማሪውም ወደጽድቅ ምድር ይመራናል ይላል (መዝ 142፥10) እንዲሁም ወደንስሐ መንገድ ኃጢአተኞችን ይመራል (መዝ 14፥8) በክርክር ጊዜም እውነቱን ይገልጻል (ማቴ 10፥20-23) መንፈስ ቅዱስ ቤተክርስቲያንን መርቶ ያደረሰበት እውነትም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። (ዮሐ 14፥6. 1ቆሮ 12፥3)

## 8.4 ለማጽናናት ወረደ፤

ዓለም ኃዘንተኛ ስለሆነ ሊያጽናና ሐዋርያትም ከኢየሱስ ተለይተው መኖር ስለማይችሉ ስለወንጌል የሚገጥማቸው ፈተናም ብዙ ስለሆነ ለማጽናናት መጣ (ዮሐ 14፥16, ዮሐ 15፥26, ዮሐ 16፥5-16) አልቃሻውን ዓለም ሊያጽናና ለመጣው ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ክብር ይሁን።

## 8.5 ስለወልድ ለመመስከር፤

ዓለም ወልድን ስላላወቀው ስለ ወልደእግዚአብሔር በሐዋርያት በቤተክርስቲያን አድሮ ለመመስከር ተገለጠ። (ዮሐ 15፥27, 1ቆሮ 12፥3)

# 9. መንፈስ ቅዱስ ወደዓለማችን በምን አምሳል ወረደ፤

## 9.1 መንፈስ ቅዱስ በበዓለ ሃምሣ የወረደው በአውሎ ነፋስ አምሳል ነው።

"ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ፣ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው።" (ሐዋ 2፥2) ተብሎ እንደተነገረ መንፈስ ቅዱስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ የተገለጠው በዓውሎ ነፋስ አምሳል ነበር። በብሉይ ኪዳንም እግዚአብሔር በአውሎ ነፋስና በወጀብ ውስጥ መንገድ እንዳለው ተተንብዮ ነበር እንዲህ ተብሎ "እግዚአብሔር ትዕግሥተኛ ኃይሉም ታላቅ ነው፤ በደለኛውንም ንጹሕ ነህ አይልም እግዚአብሔር በወጀብና በዐውሎ ነፋስ ውስጥ መንገድ አለው ደመናም የእግሩ ትቢያ ነው" (ናሆም 1፥3) እግዚአብሔር በነቢዩ የተናገረውን ትንቢት ለመፈጸምና ለማከናወን በአውሎ ነፋስ አምሳል ተገልጦአል። ነፋስም የመንፈስ ቅዱስ ምሣሌ እንደሆነ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተናግሮአል። (ዮሐ 3፥8) ከዚህ በተረፈ በነፋስ ለምን እንደተመሰለ በሌላ ክፍል እንመለከታለን።

## 9.2 በአምሳለ እሳት ወረደ፤

መንፈስ ቅዱስ በንጹሐን ሐዋርያት ላይ የወረደው በአውሎ ነፋስ አምሳል ብቻ አልነበረም። እንደወርቅ ሊያጠራቸው በእሳት አምሳል ነበር እንጂ "እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው በእያንዳንዳቸውም



ላይ ተቀመጡባቸው" (ሐዋ 2፥3) የሚለው ቃለ እግዚአብሔርም ግልጽ የሚያደርገው ይህንኑ ነው እሳትም የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ መሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጧል (ማቴ 3፥11) ማብራሪያውን ስለመንፈስ ቅዱስ ምሳሌዎች በተነገረበት ክፍል ይመልከቱ።

# 10. መንፈስ ቅዱስ ለሕይወታችን፤

መንፈስ ቅዱስ ለሕይወታችን ሕይወት ነው። ቀዳማዊ አዳምን ከፈጠረ በኋላ እግዚአብሔር ለሰዎች ሕይወትን የሰጠው እፍ በማለት በመለኮታዊ እስትንፋሱ ነበር። ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው የሆነው በመንፈስ ቅዱስ ሕይወትነት ነበር። (ዘፍ 2፥7) ይመልከቱ። ኢዮብም "የእግዚአብሔር መንፈስ ፈጠረኝ ሁሉን የሚችል የአምላክ እስትንፋስ ሕይወትን ሰጠኝ።" (ኢዮ 33፥4) በማለት የተናገረው ይህንኑ ከላይ የጠቀስነውን በጥንተ ፍጥረት መንፈስ ቅዱስ ለሰው ልጅ ሕይወትን ሰጭ መሆኑን ነበር።

በበደል ምክንያት የሰው ልጅ ንጽሐ ጠባይዕ ካደፈ በኋላ እንደገና የተነሳቀለው መንፈሳዊ ሕይወት የታደሰው የተቀደሰው በመንፈስ ቅዱስ ነው። ከዚህ የሚከተሉት የሐዲስ ኪዳን ቃላትም ግልጽ የሚያደርጉት ይህንኑ እውነት ነው። ቅ/ጳውሎስ ንጽሐ ጠባዕያችን የታደሰው ሁለተኛ የተወለድነው በመንፈስ ቅዱስ ነው ይለናል (ቲቶ 3፥5) ባለቤቱ ደግሞ ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለድን ሕይወት እንደሌለን ተናግሮ ሁለተኛ ተወልደን ሕይወትን የለበስንበት መንፈስ መንፈስ ቅዱስ ነው ይለናል (ዮሐ 3፥3-8)

10.1 ክርስቶስን በማመን ዳግም ተወልደንበታል (ቲቶ 3፥5, ዮሐ 3፥3-8)

10.2 በመንፈስ ቅዱስ የክርስቶስ ቤተሰቦች ሆነናል፤

ይህንን በተመለከተ ሐዋርያው ቅ/ጳውሎስ "አይሁድ ብንሆን የግሪክ ሰዎችም ብንሆን ጨዋዎችም ብንሆን እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናልና። ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል።" (1ቆሮ 12፥13) በማለት የሚገልጽልን ይህንኑ ነው። ቤተክርስቲያን (ምዕመን) በመንፈስ ቅዱስ አንድ የኢየሱስ ክርስቶስ አካል ቤተሰብ ናት።

የሰው ዘር ሁሉ በክርስቶስ ካመነ ባሪያም ቢሆን ጨዋም ቢሆን ወንድም ቢሆን ሴት ትልቅም ትንሽም ቢሆን ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ አንድ አካል አንድ ቤተሰብ ነው።

## 10.3 በሕይወታችን ይኖራል፤

አምነን የተቀበልነው የእግዚአብሔር መንፈስ (1ቆሮ 2፥12) በሕይወታችን ውስጥ ይኖራል፤ በውስጣችን መንፈስ እግዚአብሔር ለመኖሩ ሐዋርያው የሚከተለውን እንዲህ በማለት ጽፏል። "የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ እንደሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን?" (1ቆሮ 3፥16) ከዚህ ላይ ሐዋርያው እንደጠቆመን ሁላችን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያዎች ነንና ሰውነታችንን በቅድስና ልንጠብቀው እንደሚገባ ሲሆን በተጨማሪም የእግዚአብሔር መንፈስ የሚኖርበት አካላችንን በኃጢአት በጣዖት ብናረክሰው ብናፈርሰው እኛነታችንን በመዓት እግዚአብሔር እንደሚያፈርስ በቁ.16 የማስጠንቀቂያ ቃል ተጽፏል።

ክርስቲያን ወንድሜ አባቴ እናቴ እኅቴ ሆይ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ የሆነውን አካላችንን ከጣዖት፣ ከገለሙት፣ ከርኩሰት፣ ከስካር፣ ከመዳራት . . . ጠብቀነዋልን? በውስጣችን ያደረውን መንፈስ ቅዱስን አላስመረርነውምን? እርሱ ቅዱስ መንፈስ ነውና እኛ ግን ከንቱና ርኩስ



ሥራ ከሠራን መንፈስ ቅዱስ አብሮን ሊኖር አይችልም መቅደሱን አሳድፈነዋል ከማሳደፍም አልፎ አፍርሰነዋልና።

## 10.4 ለመዳን ሕይወታችን ታትሞበታል መንፈስ ቅዱስ የሕይወታችን ማኅተም ነው፤

ማኅተም የሚባለው ብዙ ነገሮችን ያመለክታል። ለምሳሌ የሚከተሉትን እንመልከት። አለመርሳት አለመዘንጋትን እንደማስታወሻ ጽፎ ቆጥሮ ማኖርን ያመለክታል፤ ኢዮብ ኃጢአቱም ሆነ ጽድቁ በእግዚአብሔር ፊት የማይዘነጋ መሆኑን ሲገልጽ ማኅተም የሚለውን ቃል ተጠቅሟል (ኢዮ 14፥7)

ሌላው ደግሞ ያለን ነገር መጋረድን ወይንም ማሳለፍንም ያመለክታል (ኢዮብ 9፥7) ራዕይን ምሥጢረ እግዚአብሔርን መሸሸግን ያመለክታል (ዳን 8፥26, ራዕይ 10፥4) ማኅተም ስም የተጻፈበት ዓርማ መለያ ያለው ሊሆን ይችላል በጣት ቀለበትም ሊከናወን ይችል እንደነበር ተጽፏል (ዳን 6፥17)። በአጠቃላይ ማኅተም የታተመ ወረቀት ሥልጣንን የመስጠት (ዘፍ 41፥42) ባለቤትነትን ሊያረጋግጥ የሚችል (ኤር 32፥10-14) ምሥጢራዊ ምልክት ነው በአንድ ባለሥልጣን ማኅተም የታተመ ወረቀት የማይለወጥ ውሳኔን የያዘ መሆኑ ግልጽ ነው። በመሆኑም በባለሥልጣን ማኅተም የታተመ ነገር አይለወጥም (አስቴ 8፥8, ዳን 6፥17, ማቴ 27፥66) ከላይ እንደተመለከተው በራዕይና በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት ለተጻፉ የትንቢት ቃላትም ማኅተም የታተመባቸው ምሥጢር በመሆናቸውና(ኢሳ 29፥11, ዳን 12፥9, ራዕይ 5፥9-10) በጊዜው ስለሚገለጡ ነው። (ራዕይ 22፥10) (የመጽሐፍ ቅዱስ መገለገበ ቃላት)፡

ከላይ በተመለከትነው ማብራሪያ ማኅተም ምን እንደሆነ በመጠኑ ከተገነዘብን መንፈስ ቅዱስ ማኅተም ነው። መንፈስ ቅዱስ ማኅተማችን

ነው። በመንፈስ ቅዱስ ማኅተምነት ታትመናል ስንል ምን ማለታችን ነው። ንብረትነታችን የእግዚአብሔር ነው። ማንኛውም በእግዚአብሔር ልጅ አምኖ የተጠመቀ ሁብተ ወልድና ስመክርስትና የተሰጠው ክርስቲያን የእግዚአብሔር ነው ማለታችን ነው፡ በመንፈስ ቅዱስ ስለመታተማችን የሚያወሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች (2ቆሮ <u>1፥22</u>, ኤፌ <u>1፥13</u>, ኤፌ <u>4፥30)</u> እና ሌሎችም ናቸው።

"ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ አታሳዝኑ" (ኤፌ <u>4፥30)</u> ይላል።

አንባቢ ሆይ የታተምክበትን መንፈስ አታሳዝነው ከማኅበረ አጋንንት የተለየህበት ነጻነትህን የተጎናጸፍክበት ሞትን ድል የምትነሣበት፣ ዓለምን የምታሸንፍበት የእግዚአብሔርነትህ የሚረጋገጥበት መለያህ ክብርህ እርሱ ነውና አታሳዝነው እርሱ የእምነት መንፈስ ስለሆነ ከመናፍቃን ጋር ስትሄድ ያዝናል እርሱ የቅድስና መንፈስ ነውና ከርኩሳን ከዘማዎች ጋር ስታብር ዕድል ፈንታህን ከዘማዎች ጋር ስታደርግ ያዝናል። እርሱ ጻድቅ ነውና ከክፉዎች ጋር በክፉት አንድ ስትሆን ያዝናል። እርሱ አዳኝ ፈዋሽ መንፈስ ነውና ወደጠንቋይ ስትሄድ ተስፋህ ፈጣሪ ሳይሆን ፍጡር ሲሆን ያዝናልና በእነዚህና ተዘርዝረው በማያልቁ ሌሎችም ኃጣውዕ አታሳዝነው።

## 10.5 <u>በጸጋው ባዕነታችንን የሚሞላ የጸጋ መንፈስ በመሆኑ በጸጋው ያስጌጠናል፤</u>

ከዚህ ቀጥሎ የምንመለከታቸው መጽሐፍ ቅዱሳውያን ቃላትም የሚያንጸባርቁት ይህንኑ ነው።



"የጸጋም ሥጦታ ልዩ ልዩ ነው መንፈስ ግን አንድ ነው" (1ቆሮ <u>12፥4</u>) "አሠራርም ልዩ ልዩ ነው ሁሉን በሁሉ የሚያደርግ እግዚብሔር ግን አንድ ነው። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል። ለአንዱ ጥበብን መናገር በመንፈስ ይሰጠዋልና፣ ለአንዱም በዚያው መንፈስ እውቀትን መናገር ይሰጠዋል፣ ለአንዱም በዚያው መንፈስ እምነት ለአንዱም በአንዱ መንፈስ የመፈወስ ስጦታ ለአንዱም በዚያው ተአምራት ማድረግ ለአንዱም ትንቢት መናገር፣ ለአንዱም መናፍስትን መለየት፣ ለአንዱም በልዩ ዓይነት ልሳን መናገር፣ ለአንዱም በልሳኖች የተነገረውን መተርጐም ይሰጠዋል ይህን ሁሉ ግን ያ አንዱ መንፈስ እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል።" (1ቆሮ <u>12፥6-11)</u>

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎች ቤተክርስቲያን ተቀብላ ራሷን ያስጌጠች መሆኗን ልብ እንበል። ቤተክርስቲያን ማለት በአዳም በደል ጸጋው ከተነሣው በኋላ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በረከት የተቀበለች የሰው ልጆች ኅብረት ማለት ናት። በመሆኑም መንፈስ ክርስቶስ መንፈስ ቅዱስ ቤተክርስቲያንን አከበራት ከፍ ከፍ አደረጋት አገነናት።

## 10.6 <u>*እንዴት መጸለይ እንዳለብን ስለማናውቅ በውስጣችን ሆኖ እንደእግዚአብሔር ፈቃድ እንድንጸልይ ያደርጋል (ሮሜ 8፥26)*</u>

እርሱ አባ አባት ብለን ወደ እግዚአብሔር የምንጮህበት ቅዱስ መንፈስ (መንፈሰ ልደት) የልጅነት መንፈስ ነውና (ገላ 4፥6)

## 10.7 ሕይወታችንን ወደ እውነት ይመራል፤ (ዮሐ 16፥13)

ቅድመ ርደተ መንፈስ ቅዱስ የሰው ልጆች ጸሎት "ወመንፈስከ ቅዱስ ይምርሐኒ በምድረ ጽድቅ" ሲተረጎም "ቅዱስ መንፈስህ ወደ ምድረ ጽድቅ ይምራኝ" የሚለው ነበር (መዝ141፥10) በመሆኑም ወደ እውነት የሚመራን መንፈስ ተገለጠ ዛሬ ሁላችን በዚህ መንፈስ ምሪት ልንኀዝ ያስፈልጋል። "በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው።" ተብሎ ተጽፎአልና (ሮሜ 8፥14)

## 10.8 የሕይወታችን መምህር ነው፤

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ቅዱስ የሕይወታችን መምህር መሆኑን ሲገልጽልን "አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነ አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል። እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል" (ዮሐ 14፥26) በማለት ለደቀመዛሙርቱ ተናገረ ከዚያ አስቀድሞም "መንፈስ ቅዱስ በዚያች ሰዓት ልትናገሩት የሚገባችሁን ያስተምራችኋልና" (ሉቃ 12፥12) በማለት ስለወንጌል ስለክርስቶስ በባለሥልጣኖች ፊት ስለሚናገሩት ነገር እንደሚገልጽላቸው ተናግሮ ነበር ቅ/ጳውሎስም ስለቤተክርስቲያን ዕውቀት "እኛ ግን ከእግዚአብሔር እንዲያው የተሰጠንን እናውቅ ዘንድ ከእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ እንጂ የዓለምን መንፈስ አልተቀበልንም" (1ቆሮ 2፥12) በማለት ተናግሯል።

ቤተክርስቲያን ስለኢየሱስ ጌትነት የምትመሰክረውም ከመንፈስ ቅዱስ ተምራ መሆኑን "ስለዚህ ማንም በእግዚአብሔር መንፈስ ሲናገር፦ ኢየሱስ የተረገመ ነው የሚል እንደሌለ በመንፈስ ቅዱስም ካልሆነ በቀር ኢየሱስ ጌታ ነው ሊል አንድ እንኳ እንዳይችል አስታውቃችኋለሁ።" በማለት ነበር ቅ/ጳውሎስ የገለጸው (1ቆሮ 12፥3) እንዲሁም ቅ/ዮሐንስ



ስለቤተክርስቲያን ዕውቀት ሲናገር "እናንተም ከቅዱሱ ቅባት (መንፈስ ቅዱስ) ተቀብላችኋል፣ ሁሉንም ታውቃላችሁ" (1ዮሐ2፥20-21) "እናንተስ ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት (መንፈስ ቅዱስ) በእናንተ ይኖራል ማንም ሊያስተምራችሁ አያስፈልግም ነገር ግን የእርሱ ቅባት (መንፈስ ቅዱስ) ስለሁሉ እንደሚያስተምራችሁ..." በማለት መንፈስ ቅዱስ የሕይወታችን መምህር መሆኑን ገልጾልናል።

## 10.9 ስለክርስቶስ የምንመሰክርበትን ኃይልና ጥበብ ይሰጠናል፤

"ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ።" እንደተባለ (የሐዋ 1፥8)

## 10.10 ሕይወታችንን በፍቅር ያረሰርሳል፤

"በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም" ተብሎ እንደተጻፈ (ሮሜ 5፥5, ዮሐ 4፥14. 7፥38)

## 10.11 ሰውነታችንና ውስጣዊ ሕይወታችንን በቃለ እግዚአብሔር በጸሎት የሚያጸና መንፈስ ነው፤

"በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል እንድትጠነክሩ" ተብሎ እንደተጻፈ (ኤፌ 3፥16)

## 10.12 የክርስቲያን ሕይወት መንፈሳዊ ፍሬ እንዲያፈራ ያደርጋል፤

"የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት፣ ራስን መግዛት ነው። እንደዚህ ያሉትን የሚከለክል ሕግ የለም።" (ገላ 5፥22-23) ተብሎ የተነገረውም መለኮታዊ

ቃል የሚገልጸው ይህንኑ ነው። ወንድሜ አንባቢ ሆይ መንፈስ ቅዱስ ከዚህ ላይ የተጠቀሱትን ነገሮች በአንተ ሕይወትስ አከናውኖአልን?

## 10.13 ክርስቲያኑን ከሞት ለዘለዓለም ሕይወት ያስነሣዋል፤

"ነገር ግን ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው የእርሱ መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር ክርስቶስ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው እርሱ በእናንተ በሚኖረው በመንፈሱ ለሚሞተው ሰውነታችሁ ደግሞ ሕይወትን ይሰጠዋል።" ተብሎ እንደተነገረ (ሮሜ 8፥11)

## 11. መንፈስ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ፤

ቤተክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ትመራለች፤ ቤተክርስቲያን ዮሐንስ አፈወርቅ እንደተናገረው የተወለደችው በርደተ መንፈስ ቅዱስ ነው። ቤተክርስቲያን የተወለደችውም ያደገችውም በመንፈስ ቅዱስ ነው። በመሆኑም የቤተክርስቲያን ሕይወቷ መንፈስ ቅዱስ ነው። የቤተክርስቲያን ሕይወት የሆነ መንፈስ ቅዱስም በቤተክርስቲያን ውስጥ ብዙ ሥራዎችን ያከናውናል ለምሳሌ የሚከተሉትን እንመልከት።

### 11.1 ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን ሁለተኛ ተወልዳበታለች፤

"ኢየሱስም መለሰ እንዲህ ሲል፦ እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደእግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነው" (ዮሐ 3፥5-6) ተብሎ የተጻፈው መለኮታዊ ቃል እግዚአብሔርም የሚያስገነዝበው ይህንኑ ነው።



### 11.2 ቤተክርስቲያንን ለአምልኮተ እግዚአብሔር ያነሣሣል፤

መንፈስ ቅዱስ ቤተክርስቲያንን ለእውነተኛ አምልኮት እንደሚያነሣሣና ቤተክርስቲያንም በመንፈስ ቅዱስ እንደምታመልክ መለኮታዊ ቃሉ ይጠቁመናል። "እኛ በመንፈስ እግዚአብሔርን የምናመልክ በክርስቶስ ኢየሱስም የምንመካ በሥጋም የማንታመን እኛ የተገረዝን ነንና።" (ፊልጵ 3፥3, ኤፌ 5፥18-19) ጋር ያነጻጽሩ።

### 11.3 ቤተክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ወንጌልን ትሰብካለች መንፈስ ቅዱስም በቤተክርስቲያን (በምዕመናን) ከምዕመን ጋር ወንጌልን ይሰብካል፤

"መንፈስም ፊልጶስን፦ ወደዚህ ሠረገላ ቅረብና ተገናኝ አለው" (የሐዋ 8፥23) "መንፈሱና ሙሽራይቱም፦ ና ይላሉ" ተብሎ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተጻፈ (ራዕይ 22፥7) መንፈሱ የተባለው መንፈስ ቅዱስ ሙሽራይቱም የተባለችው ማኅበረ ምዕመናን ናቸው በመሆኑም ከዚህ በላይ የተመለከትናቸው መጽሐፍ ቅዱሳውያን ምንባባትም የሚጠቁሙት ይህንኑ ሐቅ ነው።

### 11.4 መንፈስ ቅዱስ የቤተክርስቲያንን መሪዎች ይሾማል፤

"በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ" (ሐዋ 20፥28) ዛሬም ነገም ቢሆን መንፈስ ቅዱስ ባልመረጣቸው በሥጋዊ አሠራር በተመረጡ ሰዎች የምትመራ ቤተክርስቲያን ወደእውነት ለመድረስ አትችልም፣ መሪዎቿ በመንፈስ

ቅዱስ አልተሾሙምና ስለዚህ እንደቀደሙት አባቶቻችን ሹመት ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ሊሆን ይገባል (የሐዋ 1፥25-26, 13፥2)

## 11.5 መንፈስ ቅዱስ ለቤተክርስቲያን የወደፊቱን ክፉም ሆነ በጎ ነገር ይገልጥላታል፣ ይመራታል፣ ያስጠነቅቃታል፤

"መንፈስ ግን በግልጥ፦ በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያዳመጡ ሃይማኖትን ይክዳሉ ይላል፤ በገዛ ኅሊናቸው እንደሚቃጠሉ ደንዝዘው እነዚህ ውሸተኞች መጋባትን ይከለክላሉ፣ አምነውም እውነትን የሚያውቁ ከምስጋና ጋር ይቀበሉ ዘንድ እግዚአብሔር ከፈጠረው መብል እንዲርቁ ያዝዛሉ።" (1ጢሞ 4፥1-3) የሚለውን መልእክት መንፈስ ቅዱስ በግልጽ እንደተናገረ አሁን ካነበብነው ጥቅስ መረዳት ይቻላል።

## 11.6 ውሳኔዋን መንፈስ ቅዱስ ለቤተክርስቲያን ያስተካክልላታል፤

"ለጣዖት ከተሠዋ፣ ከደምም ከታነቀም፣ ከዝሙትም ትርቁ ዘንድ ከዚህ ከሚያስፈልገው በቀር ሌላ ሸክም እንዳንጭንባችሁ እኛና መንፈስ ቅዱስ ፈቅደናልና። ከዚህ ሁሉ ራሳችሁን ብትጠብቁ በመልካም ትኖራላችሁ ጤና ይስጣችሁ።" (ሐዋ 15፥28-29) ተብሎ እንደተጻፈ የሐዋርያት ሁለተኛ ሲኖዶስ ውሳኔ የተጠናቀቀውና ውሳኔው የጸደቀው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት መሆኑን አንባቢ ልብ ይላል።

ከዚህ በተጨማሪ ቤተክርስቲያን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስትሄድ ይባርካታል ለእግዚአብሔር አልገዛ ስትል ደግሞ ይገሥጻታል ይህንንም እውነት በእስያ ለነበሩት ሰባት አብያተ ክርስቲያናት መንፈስ ቅዱስ በላከው መልእክት ይታወቃል (የዮሐንስ ራዕይ ም 2-3 ልብ ብለው



ያንብቡ) በእያንዳንዱ መልእክት መዝጊያ ላይ "መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ" የሚል ቃል ተጽፏል።

# 12. የመንፈስ ቅዱስ ምሣሌዎች፤

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ በልዩ ልዩ ነገሮች ተመስሏል ነገር ግን የተመሰለባቸው ነገሮች መንፈስ ቅዱስ ናቸው ማለት አይደለም። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ የተመሰለባቸው ምሳሌዎች ናቸው። ከተመሰለባቸው ምሳሌዎች ጥቂቱን ብንጠቅስ፦

## 12.1 በነፋስና አውሎ ነፋስ፤

መንፈስ ቅዱስ በነፋስ መመሰሉ ነፋስ ነው ማለት አይደለም ነገር ግን ጌታችን እንደመሰለው ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል ድምፁም ይሰማል ነገር ግን ከወዴት እንደመጣ ወዴትም እንደሚሄድ እንደማይታወቅ ሁሉ ጸጋ መንፈስ ቅዱስም ሆነ ራሱ መንፈስ እግዚአብሔር ሰው ላይ ሲያድር አይታይም አይታወቅም ነፋስ ዛፍን ሲያንቀሳቅስ ባሕርን ሲያናውጥ ይታያል እንጂ መልኩ እንዳይታይ መንፈስ ቅዱስም ምሥጢር ሲገልጽ ቋንቋን ሲያናግር ይታወቃል እንጂ በሰዎች ሲያድር አይታወቅምና። ነፋስ (አየር) ለሕይወት አስፈላጊ እንደሆነ ሁሉ ያለ አየርም ሕይወት ያለው ፍጥረት ሁሉ በሕይወት መኖር እንደማይችል እንደዚሁ ሁሉ ያለመንፈስ ቅዱስም ክርስቲያናዊ ሕይወት የለምና። "እስመ ነፋስ ይስሕቦ ለቁመተ ሥጋን" ነፋስ ሥጋዊ አካላችንን ያሳድጋል ተብሎ እንደተጻፈ መንፈስ ቅዱስም ቁመተ ነፍሳችንን ያሳድጋልና "እስመ ነፋስ ያገዝፎ ለፍሬ" ነፋስ ፍሬን ያሳድጋል። "እስመ ነፋስ ነፍሳቲሆሙ ለማያት - ነፋስ የውኃዎች ሕይወት ነው።" ተብሎ እንደተጻፈ በመንፈሳዊ ፍሬ የብስ (ደረቅ) እኛነታችንን የሚያስጌጥ ሕይወተ ሥጋ ሕይወተ ነፍስን የሚያድል ስለሆነ በነፋስ ይመሰላል። ለማስረጃ "ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል ድምፁንም ትሰማለህ ነገር ግን

ከወዴት እንደመጣ ወዴትም እንዲሄድ አታውቅም ከመንፈስ የተወለደ ሁሉ እንዲሁ ነው" (ዮሐ 3፥8) ተብሎ የተጻፈውን ልብ ይበሉ። በአውሎ ነፋስም ይመሰላል ሉቃስ ስለርደተ መንፈስ ቅዱስ ሲጽፍ እንደገለጸልን ፍሬን ከገለባ ስለሚለይ በነፋስ በአውሎ ነፋስ ይመሰላል።

## 12.2 *በእሳት ይመሰላል፤*

"ወውዕቱ ያጠምቀክሙ በመንፈስ ቅዱስ ወበእሳት - እርሱ በመንፈስ ቅዱስ እሳትነት ያጠምቃችኋል" የሚለውን ቃለ ወንጌል ሲተረጉሙ፡- ስለመንፈስ ቅዱስ በእሳት መመሰል እንደመረጃ የሚጠቅሱትንና የሚያዛምዱብትን ነጥብ ከአበው ትርጓሜ ወንጌል የተገለጸውን ሙሉ ሐተታ ብንመለከት ምሳሌው ስለሚገባን ሐተታውን እንመልከት።

"መንፈስ ቅዱስን እሳት አለው። እሳት ምሉዕ ነው መንፈስ ቅዱስም ምሉዕ ነውና፣ እሳት በምልዓት ሳለ ቡላድን ካልመቱት አይገለጽም መንፈስ ቅዱስም ቋንቋ ሲያናግር ምሥጢር ሲያስተረጉም እንጂ አድሮ ሳለ አይታወቅምና፣ እሳት ከቡላዱ ሲወጣ በመጠን ነው ኋላ በእንጨት እያቀጣጠሉ ያስፋፉታል መንፈስ ቅዱስም በጥምቀት ሲሰጥ በመጠን ነው ኋላ በሥራ ያስፋፉታልና፣ እሳት ጣዕምን መዓዛን ያመጣል መንፈስ ቅዱስም ጣዕመ ጸጋን መዓዛ ጸጋን ያመጣልና፣ እሳት በመጠን ቢሞቁት ሕይወት ይሆናል። ከመጠን ወጥቶ የሞቁት እንደሆነ ግን ያቃጥላል መንፈስ ቅዱስም በሚገባ በተጻፈው የመረመሩት እንደሆነ ሕይወት ይሆናል። በማይገባ ከተጻፈው ወጥቶ የመረመሩት እንደሆነ ግን ይቀስፋልና፣ እሳት በላዒ ለዓማፅያን ለእለ ይክሕዱ ስሞ ወእሳት ማሕየዊ ለርቱዓነ ልብ ለእለ ይገብሩ ፈቃዶ ትርጉሙ ስሙን ለሚክዱ ዓመፀኞች ሰዎች የሚባላ እሳት ነው ፈቃዱን ለሚሠሩ ልቡናቸውን ላቀኑ ሰዎች የሚያድን እሳት ነው እንዳለ (ቅዳሴ ማርያም) እሳት ያቀረቡለትን ሁሉ



ያቃጥላል መንፈስ ቅዱስም ሕዝብ አሕዛብ የጸለዩትን ጸሎት ያቀረቡለትን መሥዋዕት ይቀበላልና፣ እሳት ውኃ ገደል ካልከለከለው ሁሉን ላጥፋ ቢል ይቻለዋል፣ መንፈስ ቅዱስም ቸርነቱ ካልከለከለው ሁሉን ላጥፋ ቢል ይቻለዋልና፣ እሳት ዱር ይገልጣል፣ መንፈስ ቅዱስም ምሥጢር ይገልጣልና፣ እሳት የበላው መሬት ለእህል ለተክል ያመቻል መንፈስ ቅዱስ ያደረበት ሰውነት ለገድል ለትሩፋት ያመቻልና እሳት ከዛኅላቸው (ከገለገታቸው) ሳይሣተፍ ሰባቱን ማዕድናት ያጠራቸዋል፣ መንፈስ ቅዱስም ከግብራቸው ሳይሳተፍ ሁሉን ያነጻልና "ይእቲ ታነጽሕ ወኢትረስሕ" እንዲል እሳት ከአንዱ ፋና አምሳ ስልሳ ፋና ቢያበሩበት ተከፍሎ የለበትም። መንፈስ ቅዱስም ተከፍሎ ሳይኖርበት እስከ ምጽአት ድረስ ሲሰጥ ይኖራልና "ይእቲ ትሁብ ወኢትቀብል" እንዲል። በእሳት ቀድሞ ሰብአ ሰዶም ሰብአ ገሞራን ከእስራኤል አንዱን ኀብር አጥፍቶበታል ለመዓት እንጂ ለምሕረት አልተፈጠረም እንዳይሉ ለምሕረት እንደተፈጠረ ለማጠየቅ። አንድም ሸክላ ሠሪ ሠርታ ስትጨርስ ነቅ ያገኘበት እንደሆነ እንደገና መልሳ ከስክሳ በውኃ ለውሳ በእሳት ታድሰዋለች ተሐድሶም በመንፈስ ቅዱስ ነውና።

ከዚህ ላይ የተመለከትነው የአበው ማብራሪያ ስለመንፈስ ቅዱስ በእሳት መመሰል በቂ ማስገንዘቢያ ይሰጠናል፡ በተጨማሪ ስለርደተ መንፈስ ቅዱስ ቅ/ሉቃስ የተናገረውን (የሐዋ 2፥2-3) ስንመለከት በእሳት ላንቃ አምሳል መሆኑም ከዚህ የራቀ ትርጉም የለውምና ከላይ የተሰጠውም ከቀደመው ጋር አንድ ነው (አንድምታ ወንጌል ይመልከቱ)።

## 12.3 ሌሎች የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌዎች፤

በእግዚአብሔር ጣት (ሉቃ 11፥20) በውኃ (ዮሐ 7፥37-39) ዘካ (14፥8. ሕዝ 47፥1-5, ኢሳ 55፥1-6,) በርግብ (ማቴ 3፥16, ዘፍ 8፥8-12) በማኅተም (2ቆሮ.1፥22, ኤፌ 1፥13-14, 4፥30) ተመስሎ ይገኛል።

## 13. የመንፈስ ቅዱስ አካላዊነት ስለተገለጸባቸው አካላዊ ቋንቋዎች፤

መንፈስ ቅዱስ አካላዊ እንደመሆኑ ከአብ ከወልድ ጋር እኩል የሆነ ፈቃድ እንዳለው በ1ቆሮ 12፥11 መጻፉ አካላዊነቱን ይገልጻል። ከእርሱ ፈቃድ ውጪም አንድ ነገር እንኳ እንዳይፈጸም አካላዊና ሁሉን ቻይ በመሆኑ ይከለክላል (ዮሐ 16፥6-7) አካላዊ ነባቢ በመሆኑ ይናገራል። (ሐዋ 28፥25, ራእይ 2፥7, 3፥13-22) አካላዊ እንደመሆኑ ከአብ ከወልድ ጋር አንዲት ስምረት አላቸው። ሰዎችንም ይወዳል (ሮሜ 8፥30)

## 14. መንፈስ ቅዱስ ከሕይወታችን እንዳይለይ መደረግ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች፤

እንግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እንዳይለየን አንቃወመው አናሣዝነው (ኤፌ4፥30) ከሕይወታችን እንዲርቅ አናድርገው (አናጥፋው) (1ተሰ5፥19) አንስደበው (ማቴ.12፥32-33) አንዋሸው ሰው ሊዋሸው አይችልምና። (የሐዋ 5፥3)

አንባቢ ሆይ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ለመሆን ጸልይ
እግዚአብሔር ከሁላችን አይለይ
አሜን



## ጥያቄዎች

1. መንፈስ ቅዱስ ማን ነው?
2. እንዴት ዓለማትን ፈጠረ?
3. የስም ልዩነቱ እንዴት ነው?
4. የመንፈስ ቅዱስ መገለጫ ተነባቢ መገለጫ ስሞቹ ማን ማን ናቸው?
5. መንፈስ ቅዱስ በበዓለ ሃምሳ ለምን ወረደ?
6. መንፈስ ቅዱስ በበዓለ ሃምሳ በምን አምሳል ወረደ?
7. መንፈስ ቅዱስ በበዓለ ሃምሳ ለሕይወታችን በሕይወታችን ውስጥ ምን ይሠራል?
8. መንፈስ ቅዱስ በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚያከናውናቸውን ነገሮች ዘርዝር።
9. የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌዎች ምን ምን ናቸው?


መምህር ልዑለ ቃል አካሉ ዓለሙ
መ.ሣ.ቁ. 270
አዲስ አበባ
Leulekal Akalu Alemu
266 Robbin Street
Decatur G.A. 30030
U.S.A.